## ዕፁብ ነው ግርማው

ዕፁብ ነው ግርማው

ድንቅ ነው ሥራው

ግርማው ዕፁብ ጌታ ሰላም አስከባሪ

በጸሎት እንጓዝ አምላክ አለን መሪ

ወዳጁን ይመርጣል ታላቁ ፈጣሪ

መጠነቅ አያውቅም ጸሎት አዘውታሪ

ብሩክ ሲል ሲቀድስ ታላቁ መሐሪ

አክብሮ ይዞታል የቅዱሳን አኩሪ

አዝ . . . . .

> መሬቱ ክቡር ነው ሰማዮ ቅዱስ
>
> በቃሉ አጽንቶታል ወገኑን ሊያድስ
>
> ሰውን አዘጋጀው ሠራው በመንፈስ

አዝ . . . . .

> እምነት አስታጠቀው የብሱን እንዲወርስ
>
> በቀጠሮ መጣ ተወልዶ ኢየሱስ
>
> ዓለሙን ተጽናና ገነትን ለመውረስ

አዝ . . . . .

> መጨነቅ ቀረለት መንቀጥቀጥ ዓለም
>
> መንፈሱ ረክቶለት ኖረ በሰላም
>
> እጅግ አይደንቅም ወይ በአምላክ መጠቀም